**<u>ጠቅላላ እይታ</u>**

ኤተርየስ ሶሳይቲ አለም አቀፍ መንፈሳዊ ወንድማማችነት ሲሆን በዋናነት ስለ ሰው ልጅ መንፈሳዊ ነፃነት እና ብቃት ላይ በተመለከተ ይሰራል፡፡

ሶሳይቲው የተመሰረተው እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር በ1955 የዮጋ መምህር በሆኑት በዶክተር ጆርጅ ኪንግ አማካኝነት ነው፡፡ በሶሳይቲው የሚሰጡት ዋና ዋና ትምህርቶችም የተገኙት ዶክተር ጆርጅ ኪንግን እንደ ማስተላለፊያ መሳሪያ በመጠቀም በመንፈሳዊ ደረጃቸው እጅግ ከረቀቁ በዚህና በሌሎች አለማት ከሚገኙ ታላላቅ መምህራን ነው፡፡

እነዚህ ጥበቦች ከዚህ በፊት እንደነ ስሪ ክርሽና ፣ ቡድሃ እና እየሱስ ባሉ ታላላቅ የሰማየ ሰማያት መምህራን ለሰው ልጅ የተሰጡትን ትምህርቶች ለመተካት ሳይሆን ነገር ግን በነባሩ ይዘት ላይ የሰማየ ሰማያት እውቀቶችን ባካተተ መልኩ የተሰጡ ናቸው፡፡

የሶሳይቲወም አንዱና ዋነኛው እምነት እነዚህ ባለፉት ጊዜዓት ወደ መሬት መጥተው የነበሩት ታላላቅ መምህራን ብዙዎቹ ከሌላ አለማት የመጡ ናቸው የሚል ነው፡፡

የሶሳይቲው ትምህርት በዋናነት ከራስ ይልቅ ለሌሎች የማገልገልን አስፈላጊነት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ መርህ ቃሉም እንደሚገልፀው፡-

**"አገልግሎት በፅድቅ ማማ ላይ ያለች ጌጥ ነች"**

ሶሳይቲው እራሱን እንደ አንድ እና ብቸኛ የፅድቅ እና የመንፈሳዊው ብቃት መድረሻ መንገድ አድርጎ አያቀርብም፡፡ ይልቁንም የሁሉም ትላልቅ ሃይማኖት መርሆች በተለያየ መልኩ የሚመሰክሩት ስለ አንዱ እና ጊዜ ስለማይሽረው መለኮታዊውና የሁሉ ምንጭ ስለሆነው እውነታ ነው ብሎ ያምናል፡፡

የሶሳይቲው አርማ ምልክት ትርጉም እግዚአብሄር ጥበብን ተመስሎ ሲከሰት የሚል ነው፡፡ በስተግራ ያለው ጥንታዊና ቅዱስ ምልክት እግዚአብሄርን የሚወክል ሲሆን በስተቀኝ የሚገኘው የሶስት መዓዘን ምስል ምልክት ደግሞ ጥበብ የሚለውን ይወክላል፡፡

## <u>መሰረታዊና ቁልፍ እምነቶች</u>

የሶሳይቲው እምነት እነዚህ የሚከተሉትን ጉዳዮች በሰፊውና በጥልቀት ይሸፍናል፡፡ፍልስፍና፣ ሃይማኖት፣ ሜታ ፊዚክስ (የነገሮች እውነታን የሚመረምር እና የሚያስረዳ) እንዲሁም የመንፈሳዊ ጥናት እና ምርምር ናቸው፡፡

በተጨማሪም የሚከተሉትን ቁልፍ ሃሳቦችንም ያካትታል፡፡

## <u>ከራስ ይልቅ ለሌሎች መርዳትን ያማከለ አገልግሎት</u>

ሌሎችን ማገልገል (ካርማ ዮጋ) ማንም ሰው ሊከውነው የሚችል ትልቅ መንፈሳዊ ልምምድ ነው፡፡ ይህም በኤተርየስ ሶሳይቲ ትምህርት እና ስራ አካሄድ ላይ የግንባር ቀደምትነቱን ቦታ ይይዛል፡፡

## <u>ዮጋ</u>

ዮጋ ለሌላው መስጠትን መሰረት ማድረጉ እንዳለ ሆኖ ለአካል ብቃት ፣ እራስን ለማዝናናት እና ጤናን ከመጠበቂያነት ባለፈ ወደ መንፈሳዊ ብቃት እንደሚያደርስ የተረጋገጠለት ጥንታዊ መንገድ ነው፡፡

## <u>መንፈሳዊ ሃይል፡ ፀሎት እና ፈውስ</u>

መንፈሳዊ ሃይል በተፈጥሮ ህግ መሰረት እንደ ኤሌክትሪክ በተጨባጭ የሚሰራ ሃይል ነው፡፡ ለተላከለት ነገር ሁሉ ሊፈውስ የመንፈሳዊ ተመስጦ እና ምሪት ሊሰጥ ሊባርክ እና ከክፉ ነገር ሊከላከል ይችላል፡፡

ይህንን ብርሃን እና ፍቅር ሃይል ሁላችንም ወደራሳችን ማምጣት እና ለሌላው ማስተላለፍን መማር እንችላለን፡፡ ይህ ብቻ አይደለም በዚህ ሃይል እራሳችንን እና ሌሎች ግለሰቦችን ከሁሉም በላይ ደግሞ መላው አለምን በአንድ ላይ ለመርዳትም እንችላልን፡፡

የሃይለቃል ፀሎት መልካም ተፅዕኖን ለማምጣት የመንፈሳዊ ሃይልን ወደ ራስ መሳቢያ እና ወደታለመለት ተቀባይ አካል እንዲደርስ አቅጣጫ ማስያዣ ነው፡፡

ማንትራ (አንድን ቅዱስ ቃል ደጋግሞ ድምፅን አውጥቶ መናገር) ሌላው ትልቅ የዚህን ሚስራዊ ሃይል ወደ ራስ ማምጫና ወደ ሌላውም የማስተላለፊያ መንገድ ነው፡፡ መንፈሳዊ ፈውስም በተመሳሳይ የሚሰራ ሲሆን ማንኛውም ሰው ሊማረውም ይችላል፡፡

## መለኮታዊው ማንነት

የእኛ እና የመላው ፍጥረት መሰረታዊ ማንነት መለኮታዊና የእግዚአብሄር አካል ክፍል ነው፡፡ ሁላችንም ከዚህ አንድ መለኮታዊ ምንጭ የመጣን ነን ቀስ በቀስም ወደዚሁ ምንጭ ተመልሰን እንሄዳለን፡፡

ይህም ምንጭ በተለያዩ እምነቶች ጋድ ፣ብርሃማ፣ ጅሆቫ ወዘተ በመባል በተለያየ ስም ይታወቃል፡፡

ዘላለማዊ ነው፣ ከሁሉም በላይ ሃያል ነው፣ ሁሉንም ያካተተ ነው፣ ሁሉም ቦታ ይገኛል፣ እንዲሁም ሁሉም ነገር ነው ከዚህም በላይ ነው፡፡

የህይወት ጉዞአችንን በሰላ ጥንቃቄ በመከታተል አንደኛ ከፍ ወዳለ ሰብዕና ደረጃ እንሻገራለን፡፡ ሁለተኛ ከመለኮታዊው ማንነታችን ጋር እየተዋወቅን እንሄዳለን፡፡

በዚህም የተነሳ የመንፈሳዊ ብቃት ደረጃችን እያደገ ይሄዳል ይህ ብቻ አይደለም ሌሎችን ለመርዳት የሚያስችለን መንፈሳዊ ሃይል በውስጣችን እየጨመረ ይሄዳል፡፡

## የመንፈሳዊ ልባችን ምክር እና ተፈጥሮ ያደለን ምትሃታዊ ሃይል

መንፈሳዊ የሆኑ ልምምዶችን በማድረግ እና ሌሎችን በመረዳት ውስጣችን የሚመክረንን ድምፅ በጥራት የመስማት እና አብሮን የተፈጠረውን ምትሃታዊ ሃይላችንን ማሻሻል እንችላለን፡፡

## የሌላ አለማት ህይወት

በዚህ ሶላር ሲስተም ውስጥ ባሉ ሌሎች ፕላኔቶች ላይ ከኛ እጅግ የረቀቀ ስልጣኔ ያለ ቢሆንም በአፈጣጠራቸው ልዩነት የተነሳ ግን ሳይንስ እነዚህን ፍጥረታት እስከ አሁን ሊያገኛቸው አልቻለም፡፡ነገር ግን እነዚህ ፍጥረታት ወደር በሌለው ደግነታቸው እና እራሳቸውን መስዋት በማድረግ የሰውን ዘር ተቆጥሮ በማያልቅ መንገድ እየረዱ ይገኛሉ፡፡ እነሱ ባይኖሩ ኖሮ ገና ድሮ ጠፍተን ነበር፡፡

ባለፉት ጊዜአት ከሌሎች ፕላኔቶች ትምህርት ለመስጠት እና እንዲሁም በሌሎች መንገዶች ለሰው ልጆች ወሳኝ የሆኑ እገዛዎችን ለማድረግ ከሰው ልጅ ተወልደው በመካከላችን ከተገኙት የሰማየ ሰማያት መምህራን ውስጥ እየሱስ፣ ቡድሃ፣ ስሪ ፓታንጃሊ፣ ስሪ ክሪሽና፣ ኮንፊሺየስ እና ሌዎዚ ይገኙበታል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ኤተርየስ ሶሳይቲ ከሰማየ ሰማያት መምህራን ጋር በቀጥታ በመተባበር አምስት መንፈሳዊ ተልዕኮዎችን ይፈፅማል ከእነዚህም አንዱ ዘመቻ ጸሎት ሃይል(ኦፐሬሽን ፕረየር ፓወር) ነው፡፡

የማሰብ ችሎታ ያላቸው ፍጥረቶች ከዚህም ሶላር ሲስተም ውጭ ይገኛሉ፡፡ አንዳንዶቹ ለአላማት በስልጣኔአቸው ከኛ በጣም የረቀቁ ሲሆኑ አንዳንዶቹ ደግሞ ከኛ ያነሱ ናቸው፡፡

## ዩፎ

ዩፎ ምንነቱ የማይታወቅ በራሪ ነገር በመባል ይታወቅ የነበረ ቢሆም በአሁን ጊዜ ግን የሌላ አለም ፍጥረታት የበረራ መሳሪያ መሆኑ ተረጋግጧል፡፡

እነዚህ ፍጥረታት ለዘመናት መሬትን ሲጎበኙ ኖረዋል በሂንዱ መፅሃፍት ላይ ቪማና የሚል ስያሜ ያላቸው ሲሆን በመፅሃፍ ቅዱስ ውስጥም በብዙ አይነት አገላለፅ ተቀምጠው ይገኛሉ፡፡ ለምሳሌ ደመና፣ኮከብ፣ የሚበር ጥቅል የመሳሰሉት ናቸው፡፡

## ካርማ(ድርጊት ከነአፀፋው) እና ከሞት በሃላ ዳግም መወለድ

ካርማ ትምህርት እንጂ ቅጣት አይደለም፡፡ ካርማ በመንፈሳዊ እድገት ጉዞአችን ላይ የሚያስፈልገንን ትምህርት የሚሰጠን ትልቅ መንፈሳዊ መምህር ነው፡፡

ምድር ላይ ዳግም በስጋ ተወልደን እስክንመጣ ድረስ በመሃል ባለው ጊዜ ውስጥ በሌላ የመኖሪያ ቦታ የተወሰነ ጊዜ እናሳልፋለን፡፡

ይህም ቦታ በመሬት ክፍል ውስጥ የሚካተት ሲሆን አፈጣጠሩ ግን አሁን ካለንበት የተለየ ነው፡፡ከብዙ በአካል ተደጋግሞ መወለድ በኃላ የቀረቡልንን ትምህርቶች ተምረን ስንጨርስ ይህንን ዳግም የመወለድ ኡደት ትተን ከኛ በረቀቀ ሌላ ፕላኔት ላይ በሌላ ዓይነት ኡደት የሰማየ ሰማያት መምህራን ሆነን እንኖራለን፡፡

የሰው ለጅ ለዘመናት ሲዘራው ከኖረው መጥፎ ሃሳቡና ድርጊቱ የተነሳ ሊያጭደው የተቃረበው ነገር ጥሩ አይደለም፡፡

ይሄ ደግሞ የሰማየ ሰማያት መምህራንን በብዙ መልኩ መልካም ጣልቃ ገብነታቸውን ያስቀራል፡፡ ለሰው ልጅ በከተማዎች ላይ በግልጽ እንዳይታዩ የሚያግዳቸውም ይሄው የኛው ካርማ ነው፡፡

ብዙውን የኤተርየስ ሶሳይቲ ስራ ዓላማ በዋነኛነት የዚህን አለም ዘር (ካርማ) ሚዛኑን ማሻሻል ነው፡፡በተለይም በሶሳይቲው የሚከወኑት መንፈሳዊ ተልዕኮዎች ዋነኛ መሳሪያዎቹ ናቸው፡፡

<u>ኩንዳሊኒ፡ ቻካራ እና ኦራ(ፀዳል)</u>

ብናየውም ባናየውም ቢሰማንም ባይሰማንም ሁላችንም ኦራ(ፀዳል) የሚባል በሰውነታችን የውጨኛው ክፍል ላይ የሚገኝ የብርሃን አካል አለን፡፡

ይህ ፀዳል የተሰራው ሰጋዊው አካላችን እንደተሰራበት በቀላሉ ልናየው በማንችለው ነገር ቢሆንም ይህ ማለት ግን አካላችን አይደለም ማለት ሳይሆን አፈጣጠሩ ከስጋዊ የአካል ክፍላችን የተለየ ስለሆነ ብቻ ነው፡፡

በስጋዊው አይናችን ልናየው የማንችለው ሃይል ወደ ሰውነታችን ውስጥ ከሰውነታችንም ወደ ውጭ በእነዚህ ቀዳዳዎች ወይም ቻካራወቻችን ይገባል ይወጣል፡፡

እነዚህም ሰውነታችን ላይ የሚገኙ ትናንሽ በሮች ሲሆኑ በሳይንሳዊ አጠራራቸው ፊዚክ ሴንተር በመባልም ይታወቃሉ፡፡ የጀርባ አጥንታችንን ልክ እንደ ቀጭን ግንድ ብናየው እነዚህን ትናንሽ በሮች ግንዱ ላይ እንደበቀሉ አበባዎች ሆነው የሰውነታችንን የፊተኛውና የውጨኛው ክፍል ላይ ማለትም ፡ የብርሃን አካላችን ወይም ፀዳላችን ላይ ይገኛሉ፡፡

ኩንዳሊኒ የጀርባ አጥንታችን የታችኛው ክፍል ላይ ሚገኝ ትልቅ ሚስጥራዊ ሃይል ነው፡፡ አንዳንዴ እባቡ ሃይል በመባል ይታወቃል፡፡

የዚህ ሃይል በጀርባ አጥንታችን በኩል ወደላይ መነሳት የትናንሾቹን በሮች ወይም የቻካራዎቻችንን መከፈት እና በትክክል መስራት ያስከትላል፡፡ ይኸውም ከፍተኛ ወደ ሆነ የመንፈሳዊ ብቃት ደረጃ ላይ መድረስን እና ስለ ሰማየ ሰማያት ምንነት ወደ መረዳት ይወስዳል፡፡

## የማይሞት አካል ያላቸው መምህራን

መሬት ላይ ያለ ሰው የተዘጋጀለትን ትምህርት ለመማር እና የመንፈሳዊ ስብዕና ደረጃውን ለማሳደግ በዚህ ምድር ላይ በተደጋጋሚ በአካል ይወለዳል፡፡ ይህንን የመማር ሂደት ያጠናቀቀ ግለሰብ ከፊት ለፊቱ ሁለት ምርጫዎች ይኖሩታል እነሱም፡- ከዚህ አለም በረቀቀ ሌላ አለም ላይ አዲስ የህይወት ኡደት መቀጠል ሲሆን ወይም ደግሞ የማይሞት አካል ይዞ በዚሁ አለም ላይ በመንፈሳዊ መምህርነት የሰው ልጅን እየረዳ መኖር ነው፡፡

የማይሞት አካል ያላቸው መምህራን እጅግ ታላቅ መንፈሳዊ እና ምትሃታዊ ሃይል አላቸው፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ እጅግ ታላቅ የሆነ የደግነት እና የጥበባት ባለቤቶች ናቸው፡፡ እኛ እንደምናረጀውም አያረጁም በየተወሰነ ጊዜም የሰውነት አካላቸውን በራሳቸው ፈቃድ እንደ አዲስ በመቀየር ሁሌም በአካል ወጣት እንደሆኑ ይኖራሉ፡፡

## እናታችን መሬት

እናታችን መሬት ይህን ኃላቀር እና በአብዛኛው ክፉ ለሆነው ለሰው ልጅ መኖሪያ ለመሆን ስትል የእራሷን የእድገት ጉዞ መስዋዕት ያደረገች ህይወት ብቻ ሳይሆን አምላካዊ ማንነት ያላት ፍጥረት ነች፡፡

ለማሰብ በሚያስቸግር የመስዋዕትነት ተግባር ላይ ያላቸውን እናታችን መሬትን ለመረዳት እና ለማገዝ ኤተርየስ ሶሳይቲ በብዙ መልኩ እየሰራ ይገኛል፡፡

**<u>ቅዱስ ተራሮች</u>**

እነዚህ ቅዱስ ተራሮች ከሰማየ ሰማያት ፍጥረታት እና የማይሞት አካል ካላቸው መምህራን በተለቀቀ የተለየ መንፈሳዊ ሃይል ተሞልተዋል፡፡ ይህም የሆነው በዶክተር ጆርጅ ኪንግ አማካኝነት ሲሆን ይህንን ዘመቻ ኮከብ ብርሃን የተባለውን ተራሮቹን በሃይል የመሙላት ተልዕኮ በአለም ዙሪያ ለመፈፀም ዶክተር ጆርጅ ኪንግን ከሶስት ዓመት በላይ ፈጅቶባቸዋል፡፡

ይህንን ሃይል በፀሎት አማካይነት ለማውጣት እና ወደ ተፈለገው አቅጣጫ ለማሰራጨት እንዲቻል ኤተርየስ ሶሳይቲ በዓመት ውስጥ ብዙ ጊዜ ወደ እነዚህ ተራሮች መንፈሳዊ ጉዞን ያዘጋጃል፡፡

ለተጨማሪ መረጃ : info.et@aetherius.co.uk